International Labour Organization

Improved Labour Migration Governance

UKaid from the British people

# በመካከለኛው ምስራቅ አረብ አገራትና በሊባኖስ በሚገኙ የኢትዮጵያ ሚሲዮኖችና የኢትዮጵያ ማሕበረሰብ ማሕበራት የሚሰጡ አገልግሎቶችና ድጋፎች [1]



[1] ይህ በራሪ ፅሑፍ/ብሮሸር እና መረጃ በጉዞ ስንቅ አፕሊኬሽን ላይም ማግኘት ይቻላል። ይህንን አፕሊኬሽን በአይፎንና በአንድሮይድ መገልገያዎች መጫን ይችላሉ፣ https://apps.apple.com/us/app/id1501502772 OR https://play.google.com/store/apps/details?id+com.safeway.appdev

## 1. 1. የቆንሲል አገልግሎቶች

የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንሲሎች የሚሰጡት የቆንሲላ አገልግሎቶች የሚከተሉትን ያካትታል፡-

- **የፓስፖርት ዕድሳት፡** የፓስፖርት ማደሻ ጊዜ ለደረሰባቸውና ላለፈባቸው በውጭ አገር ለሚሰሩ ኢትዮጵያውያን የዕድሳት አገልግሎት መስጠት።
- **ቪዛ፡** ኢትዮጵያውያን ላልሆኑ ዜጎች፡ የኢትዮጵያ ኢሚግሬሽን ባለሥልጣን በአብዛኛው ሁሉንም አገር የሸፈነ ቀጥታ የድረ ገፅ ቪዛ አገልግሎት መጀመሩን አሳውቋል። የጥቂት አገር ዜጎች እንደደረሱ ቪዛ ሊያገኙ ይችላሉ፣ ጎብኚዎች ለበለጠ መረጃ የኢትዮጵያን ኤምባሲዎች ወይም ቆንሲላዎች ወይም ድረ ገፃቸውን ማማከር ይኖርባቸዋል ።
- **ሰነድ ማረጋገጥ፡** ማንኛውም በአንድ አገር የተሰጠ ሰነድ በሌላ አገር ጥቅም ላይ የሚውል ከሆነ መረጋገጥ ይኖርበታል። ይህም የልደት፣የጋብቻና የሞት ሰርተፊኮቶች እንዲሁም ቀደም ሲል ወጪ ሆነው መተካት ወይም መታደስ የሚፈልጉ ሰነዶች ላይም ተፈፃሚነት ይኖረዋል።
- **ወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ፡** የጋብቻና የልደት ሰርተፊኬቶችን መመዝገብ ወይም መስጠት፣
- **የውክልና ሥልጣን፡** ኢትዮጵያውያን እንደራሳቸው ሆኖ የሚሰራ ሰው መወከል ወይም ቀደም ብሎ የተሰጠን ውክልና መሻር ከፈለጉ የውክልና ሥልጣን አገልግሎትን መጠቀም ይችላሉ፣
- **በውጭ አገር የሚሰሩ ዜጎችን ሕጋዊ ምልመላ ፣ ሥራ ስምሪትና ወደ መድረሻ አገር ጉዞ ማረጋገጥ፡** የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንሲላዎች በውጭ አገር የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች በኩል ወደ ውጭ አገር ለሥራ ስምሪት የሚሄዱ ዜጎችን ማረጋገጥና የኤጀንሲዎችን ፈቃድ ያመቻቻሉ።
- **የድጋፍ ደብዳቤ.** የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንሲሎች በውጭ አገር ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የድጋፍ ደብዳቤ፣ ለተመላሾች ከቀረጥ ነፃ የሚያደርጋቸው የድጋፍ ደብዳቤ ይሰጣሉ።
- **የመረጃ አገልግሎት.** የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንሲሎች ለኢትዮጵያውያንና ለውጭ ዜጎች ንግድን፣ ኢንቨስትመንትና የቱሪዝም ዕድሎችን የተመለከቱና

መስፈርቶቹን ጨምሮ መረጃዎች ይሰጣሉ። እንዲሁም እንደ ኮቪድ-19 እና የመድረሻ አገርን ሁኔታ የተመለከቱ ወቅታዊ ጉዳዮችን መረጃ ለኢትዮጵያ ዜጎች ይሰጣሉ።

- **ሊሴ ፓሴ፡** የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንሲላዎች በውጭ አገር ካለ ሕጋዊ ፓስፖርቶች ለሚሰሩና ወደ አገር ቤት ለሚመለሱ ወይም ተገደው ለሚወጡ ዜጎች የጉዞ ሰነዶችን አዘጋጅተው ይሰጣሉ። ለተጨማሪ መረጃ የሚቀርብዎትን የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንሲል ያማክሩ።
- **ይቅርታ፡** የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንሲላዎች የሚመለከታቸው ከመድረሻ አገሮች ባለሥልጣናት ጋር በሕገወጥ መንገድ የሚኖሩ የኢትዮጵያ ዜጎች ቅጣት ሳይከፍሉ ወይም በዕስር ሳይቀጡ እንዲወጡ እንዲፈቅዱላቸው ስምምነት ያደርጋሉ።
- **ፈቃደኛ ማሕበሮችን መደገፍ፡** የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንሲላዎች በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የሙያ፣ የንግድና ማሕበረሰብን መሰረት ያደረጉ ማሕበራት እንዲቋቋሙ ድጋፍ በማድረግ ያመቻቻሉ።

## 2. በውጭ አገር የሚኖሩ ዜጎችን መደገፍ/መርዳት

የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች፣ ቆንሲሎችና የኢትዮጵያ ማሕበረሰብ ማሕበራት በውጭ አገር ላሉና ተጋላጭ ለሆኑ ዜጎች አስፈላጊ ሀብቶች ሲገኙ የተለያዩ ድጋፎችን ያደርጋሉ። እነዚህ ድጋፎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- **መጠለያ፡** ኤምባሲዎች፣ ቆንሲሎች እና የማሕበረሰብ ማሕበራት በውጭ አገር በችግር ውስጥ ለሚገኙ የአጭር ጊዜ የማረፊያ አገልግሎት ይሰጣሉ።
- **የጤና እንክብካቤ፡** ኤምባሲዎች፣ ቆንሲሎች እና የማሕበረሰብ ማሕበሮች በውጭ አገር ለሚሰሩ ዜጎች ሕክምናና ለተጋላጮች በሆስፒታል እንዲታከሙ፣ እንዲሁም ረጅም ጊዜ በሆስፒታል ለሚቆዩ ታካሚዎች በየጊዜው የጉብኝት ፕሮግራም ያዘጋጃሉ።
- **ሞት፡** የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንሲሎች በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሲሞቱ ክትትል ያደርጋሉ።. የተቀባይ አገር ባለሥልጣናትን ለሞት ያደረሰውን መንስኤ ይጠይቃሉ እንዲሁም የቀብር ሥነስርዓቱን ወይም አስከሬኑ ወደ አገር ቤት ሚላክበትን ሁኔታ ያመቻቻሉ። የሟች የቀረ ንብረት ወይም ገንዘብ ካለ ኤምባሲው ወይም ቆንሲላው የውክልና ማስረጃ ለሚያቀርብ ለሟች ቤተሰብ እንዲተላለፍ ሁኔታዎችን ያመቻቻል።
- **የሕግ አገልግሎት፡** የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች፣ ቆንሲላዎችና የማሕበረሰቡ ማሕበራት በውጭ አገር የሚሰሩ ዜጎች ክስ ሲያጋጥማቸው ምክር፣ የሕግ የምክር አገልግሎትና የሕግ ጉዳዮች/ነገሮች ላይ ያማክራሉ። የተወሰኑ የዲፕሎማሲ ሚሲዮኖቻችን በውጭ አገር የሚሰሩ ዜጎችን በመወከል ፍርድ ቤት እንዲቀሙ የአገሩን የሕግ ባለሙያዎች የሚኖረውን አቅም መሰረት በማድረግ እንደሁኔታው (ገንዘብ ሲገኝ) ይመድባሉ/ይቀጥራሉ።
- **ማስማማት፡** የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንሲላዎች በውጭ አገር ተቀጥረው የሚሰሩ ዜጎቻችን እንደ ደመወዝ አለመከፈል፣ የሥራ ውል መቋረጥና የሥራ ሁኔታዎች እንዲሁም የኢንሹራንስ ክፍያን በተመለከቱ ጉዳዮች ከአሰሪዎቻቸው ጋር አለመግባባት ሲያጋጥማቸው በማስማማት ለመፍታት ድጋፍ ያደርጋሉ።
- **በውጭ አገር በዕስር ቤት ያሉ ዜጎች፡** የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች፣ ቆንሱላሮችና የማሕበረሰቡ ማሕበራት በዕስር ቤት ያሉ ኢትዮጵያዊ የውጭ አገር ሠራተኞች

ያሉበትን ሁኔታና ጉዳዮቻቸውን ይከታተላሉ የትርጉም አገልግሎትም ይሰጣሉ፡ ፡ እንዲሁም አገልግሎቱ በይዘቱ ውስን ሲሆን ኤምባሲዎችና ቆንሲሎች በውጭ አገር ከሚሰሩና ማሕበተረሰባቸው ጋር በመሆን በእስር ቤት ውስጥ መረዳት ያለባቸውን በየጊዜው በመጎብኘት አስፈላጊ የሆኑ እንደ ምግብ፣ልብስና የግል ንፅሕና መገልገያዎችን በመስጠት ይረዳሉ።

- **የባንክ ደብተር፡** በጥቂት አገሮች ውስጥ ያሉ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንሲሎች በኢትዮጵያ ውስጥ የባንክ ሂሳብ/ቁጥር እንዲከፈት ያመቻቻሉ፣
- **የምክር አገልግሎት፡** ጥቂት የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንሲላዎች (ለምሳሌ በዱባይ) የጋብቻ የምክር አገልግሎት እና ስለዕዳ ምክር ይሰጣሉ።

## 3. 3. ግንዛቤ ማስጨበጫ

ኤምባሲዎች፣ ቆንሲሎች እና የማሕበረሰብ ማሕበራት በውጭ አገር ለሚሰሩ ዜጎች የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን በተነሳሽነት ይሰጣሉ። ይህም የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

- **ባሕል፡** ኤምባሲዎች፣ ቆንሲሎችና የማሕበረሰቡ ማሕበራት የመድረሻ አገርን ባሕል፣ልምዶች እና የሕይወት መንገዶችን የተመለከቱ መሰረታዊ ዕውቀት ለመስጠት ተለያዩ ሚዲያዎችን ይጠቀማሉ፣
- **ማህበራዊ ክለቦች/ ስብስቦች.** ጥቂት የኢትዮጵያ ማሕበረሰቦች በውጭ አገር ለሚኖሩና አቅማቸውን በአካባቢው ቋንቋ ማሳደግ ለሚፈልጉ ኢትዮጵያውያን ትምህርትና ሥልጠና ይሰጣሉ። ብዙውን ጊዜ እነዚህ ማሕበረሰቦችና ማሕበራዊ ክለቦች ፕሮግራማቸውን
- **መብቶች፡** የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች፣ ቆንሲሎች እና የማሕበረሰብ ማሕበራት በውጭ አገር የሚሰሩ ኢትዮጵያውያን መብታቸውንና ጥቅማቸውን እንዲጠይቁ፣ እርስ በእርስ እንዲደጋገፉ፣ማሕበራዊና ባሕላዊ ዕሴቶችን ማክበርና የኢትዮጵያ የልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ መሳተፍ እንዳለባቸው ያበረታታሉ።
- **ኮቪድ-19፡** የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች፣ ቆንሲሎች እና የማሕበረሰብ ማሕበራት በውጭ አገር የሚሰሩ/የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ከኮቪድ-19 እንዴት ራሳቸውን መከላከል እንዳለባቸው መረጃና የመከላከያ መሳሪያዎችን ይሰጣሉ። ከሥራ ሲያስወጧቸውም ምግብና መጠለያ በመስጠት በመስጠት ይደግፏቸዋል።

ለበለጠ መረጃም በሚኖሩበት አገር የሚገኘውን ኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንሲል ያማክሩ ወይም ከታች ተገለፁትን ድረ ገፆች ይጎብኙ።

# ጠቃሚ አድራሻዎች

## የኢትዮጵያ የሠራተኛና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

አድራሻ: ካዛንቺስ ወረዳ 8 ቂርቆስ ክ/ከተማ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
የፖ.ሣ.ቁ.: 2056
ስልክ: +251 11 551 7080
ኢሜል: info@molsa.gov.et
ድረ ገፅ: www.molsa.gov.et

## የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

አድራሻ: አራዳ ክፍለ ከተማአዲስ አበባ ኢትዮጵያ
ፖ.ሣ.ቁ.: 1037
ስልክ: +251 11 551 7345
ፋክስ: +251 11 551 4300
ኢሜልl: MFA.Addis@ethionet.et
ድረ ገፅ: www.mfa.gov.et

## በኦማን የሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ

አድራሻ: አስ ሳሩጅ መንገድ, መንገድ ቁ. 3048 103 መስካት, ኦማን
ስልክ: +96824956487
ኢሜል: oman.mission@mfa.gov.et ወይም ethemboman@gmail.com
ወይም Muscat.embassy@mfa.gov.et
ድረ ገፅ: https://www.embassypages.com/ethiopia-embassymuscat-oman

## ጆርዳን አማን የሚገኘው የኢትዮጵያ የክብር ቆንሲል

አድራሻ: 8B ኢብራሂም ኢል ካታን መንገድ 7ኛው አደባባይ, አማን ጆርዳን
ስልክ: +96265850396
+962798806252
ድረ ገፅ: http://www.ethioconsulatejo.com/

## ሣዑዲ አረቢያ ሪያድ የሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ

አድራሻ: አቡ በከር አል ካርከሂ ሳፋራት ሪያድ 11693 ሣዑዲ አራቢያ
ስልክ: +966 11 482 3919
ኢሜል: ethembriy@gmail.com
ድረ ገፅ: https://www.twitter.com/ethioriyadh/

## ሣዑዲ አረቢያ ጅዳ የሚገኘው የኢትዮጵያ ቆንሲል

አድራሻ: ቪላ ቁ. 18,አል-አንዳለስ መንገድ ሱሌማን መስጊድ አጠገብ አል ሀምራ ወረዳ/ዞን ጅዳ ሣዑዲ አረቢያ
ስልክ: +966 12 665 3444
ኢሜል: ethcons@gmail.com
ድረ ገፅ: https://www.facebook.com/EthConsJeddah/

## ዶሐ ካታር የሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ

አድራሻ: ደብልዩ ቤይ ላጉን መንገድ ዶሐ ካታር
ስልክ: +974 4020 7000
ኢሜል: doha.embassy@mfa.gov.et ወይም ethioembassydoha@ gmail.com
ድረ ገፅ: https://ethiopiaembassyindoh.wixsite.com/ethiopia-indoha

## አቡ ዳቢ የተ.አ.ኤ. ያለው የኢትዮጵያ ኤምባሲ

አድራሻ: አል ባተን (ቁ.6) መንገድና አል ፋላህ (ቁ. 9) መንገድ ቪላ 119 23795 አቡ ዳቢ የተባበሩት አረብ ኢሜሬቶች
ስልክ: +971 2 66 551 11
ኢሜል: abudhabiethiopianemb@gmail.com ወይም abudhabiembassy@mfa.gov.et
ድረ ገፅ: www.abudhabi.mfa.gov.et

## በተ.አ.ኢ. በዱባይና በሰሜን ኢሜሬቶች የሚገኘው የኢትዮጵያ ቆንሲል ጀነራል

አድራሻ: ቪላ ቁጥር. 30, የመንገድ ቁ. 11, ማካኒ ቁ. 233-0325, አል ቁሳይስ 2

ስልክ: +971 4 269 9111 ወይም +971 4 269 9162

ኢሜል: ethcodu@ethcongen.ae ወይም contact@ethiopianconsulate.ae

ድረ ገፅ: www.ethiopianconsulate.ae

## በኩዌት የሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ

አድራሻ: ጃብሪያ Block 10, መንገድ 107, አል ኩዋይት ኩዌት

ስልክ: +965 2534 8198 / 2533 0128 or +965 2533 4291

ኢሜል: ambassador.kuwait@mfa.gov.et

ድረ ገፅ: www.kuwait.mfa.gov.et

## በቤይሩት ሊባነን የሚገኘው የኢትዮጵያ ቆንሲል ጀነራል

አድራሻ: ሀዝምየህ 67 rue 11 ML12103, ሰይድ ፍሬይሃ መንገድ አሮጌው ባንክ አውዲ ሕንፃ ቤይሩት, ሊባኖን

ስልክ: +961 5 953 656

ኢሜል: beirut.consulate@mfa.gov.et

ድረ ገፅ: www.facebook.com/www.EthioConsulateinBeirut/

## ካታር የሚገኘው የኢትዮጵያ ኮሙኒቲ ማሕበር

አድራሻ: W Bay ላጉን መንገድ ዶሃ ካታር

ስልክ: +974 30703727

ኢሜል: info@ethiocomqatar.org

## በዱባይና ሰሜን ኢሜሬቶች የተ.አ.ኢ የሚገኘው የኢትዮጵያውያን ማሕበረሰብ

አድራሻ: ቪላ ቁ. 30, የመንገድ ቁ. 11 ማካኒ ቁ. 233-0325 አል ቁሳይስ 2

ስልክ: +97142598817 ወይም +971556468202

ኢሜል: ethiocomdubai@gmail.com

## በዱባይና አካባቢዎቹ ሚገኝ የኢትዮጵያውያን ሴቶች ማሕበር

አድራሻ: ቪላ ቁ. 30, የመንገድ ቁ. 11, ማካኒ ቁ. 233-0325, አል ቁሳይስ 2

ስልክ: +971506783466

## በተባበሩት አረብ ኢሜሬቶች የሚገኙ የልጆች ማሕበረሰብ

ስልክ: +971558241770

## በአቡዳቢ, የተ.አ.ኢ. የሚገኘው የኢትዮጵያውያን ማሕበረሰብ ማሕበር

አድራሻ: መንገድ 6, አል ባቲን ማጂሊስ አጠገብ አል ባቲን አቡ ድሃቢ የተ.አ.ኢ.

ስልክ: +971 2 6658810 or +971 2 665 5111

ኢሜል: ecaadh@gmail.com

## በሊባኖን የሚገኘው ኢትዮጵያውያን ማሕበረሰብ

ስልክ: +96176783931
+96181683438

## በሪያድ ሳዑዲ አረቢያ የሚገኘው የኢትዮጵያውያን ማሕበረሰብ

ስልክ: +966535291297

## በጅዳ ሣዑዲ አረቢያ የሚገኘው የኢትዮጵያውን ማሕበረሰብ

አድራሻ: ሣዑዲ አረቢያ በጅዳ ምዕራብና ደቡብ ክልሎች የሚገኙ የኢትዮጵያውያን ማሕበረሰብ ፖ.ሣ.ቁ. 495 Jeddah 21411

ስልክ: +96603602308
+966592530033
+966551719475

## በኩዌት የሚገኘው የኢትዮጵያውያን ሕዳሴ ማሕበረሰብ

ስልክ: +96551239501

ኢሜል: ethiopiancommunity@gmail.com

በኢትዮጵያ የው.ጉ.ሚ/ር እና በሠ.ማ.ጉ.ሚ/ር ትብብር በዓለም ሥራ ድርጅት የተዘጋጀ

ጥቅምት 2020